

STAY SAFE MN

# ስለ ኮቪድ-19 ክትባት ሊያውቁት የሚገባ

ብዙዎች ስለ ኮቪድ-19 ክትባት ጥያቄም ስጋትም አላቸው። ይኽ ደግሞ የተለመደ ነው። በመሆኑም ይኽ ሰነድ ስለ ኮቪድ-19 ክትባት የበለጠ መረጃ ይሰጥዎታል።

**በኮቪድ-19 ክትባት በቀላል ሊታለፍ የሚችል የጥንቃቄ መግለጫ አይኖርም።**

- የኮቪድ-19 ክትባቶች እንደ ሌሎች ክትባቶች አስፈላጊውን የጥንቃቄ ደረጃዎች እና ጥናቶችን ያለፈ ነው። የሕክምና አጥኚዎች ክትባቱ በቶሎ እንዲሰጥ ማድረግ የቻሉት ከፌዴራል መንግሥት ቀደም ተብሎ ለጥናት ወጪ የተደረገ ገንዘብ በመኖሩ ነው።

**የኮቪድ-19 ክትባት በየትኛውም ዕድሜ ክልል ላሉ ሰዎች የተፈቀደ ነው።**

- የኮቪድ-19 ክትባት አስፈላጊው ሙከራ በአሥር ሺዎች በሚቆጠሩ በተለያዩ የዕድሜ፣ የዘር፣ የብሔር እና የጎሳ ልዩነት ባላቸው ኅብረተሰብ መካከል ተደርጎ አስተማማኝ መሆኑ ታምኖበታል።

**የኮቪድ-19 ክትባት በነፃ የሚሰጥ ነው።**

- የኢንሹራንስም ሆነ የኢሚግሬሽን ሁኔታዎ ምንም ይሁን ምን ክፍያ አይጠየቁም።

**የኮቪድ-19 ክትባት የተከታቢውን ተፈጥሯዊ ማንነት (DNA) አይለውጥም።**

- ፋይዘርም ይሁን ሞደርና የተሰኘው ክትባት የተከታቢውን የተፈጥሮ ማንነት ሊቀይር አይችልም። ምክንያቱም የተፈጥሮ ሁኔታን ሊቀይር ወደሚችለው ወደ ሰውነታችን ሴል ውስጥ አይገባም። መድኃኒቱ ሥራውን ካከናወነ በኋላ በሰውነታችን ውስጥ ይሞታል።

**ጃንሰን ጃንሰን የተባለው የኮቪድ-19 ክትባት FETAL TISSUE የለውም።**

- ክትባቱ የተቀመመው ጉዳት በማያስከትል ኮልድ ቫይረስ ነው፤ ስሙም አዴኖ ቫይረስ (ADENOVIRUS) ይባላል። ኮልድ ቫይረስ በሴላችን ውስጥ የሚያድግ እና ለአሥር ዓመታት ያህል ክትባት በሚያዘጋጁ አጥኚዎች የተሰበሰበ ነው። አብዛኛው የእምነት ሰዎች እና የሥነ-ምግባር አጥኚዎች (BIOETHICAL) ተቋም ሌሎች የኮቪድ-19 ክትባቶች በሌሉበት ቦታ ቢከተቡት የሚያስከትለው አንዳች ነገር አለመኖሩን ይናገራሉ።

**የኮቪድ-19 ክትባት ሰዎችን የሚከታተልበት (MICROCHIPS) የለውም።**

- የኮቪድ-19 ክትባት ሰዎችን ለመከታተል የሚያስችል ምንም ዓይነት (MICROCHIPS) የተባለ ንጥረ-ነገር የለውም

**የኮቪድ-19 ክትባት ምንም ዓይነት የዕንቁላል እና የአሳማ ተዋጽዖ የለበትም።**

- የኮቪድ-19 ክትባት አሳማን ጨምሮ የምንም ዓይነት የእንስሳት ተዋጽዖ የለበትም። ክትባቱም በዕንቁላል ውስጥ ያደገ አይደለም፤ በውስጡም የዕንቁላል ውጤቶችን አልያዘም።

**ነፍሰ ጡሮች ሊከተቡት ይችላሉ።**

- ነፍሰ ጡር ሴቶች በኮቪድ-19 ከታመሙ ሕመማቸው ከባድ ነው። ነገር ግን ነፍሰ ጡሮች ክትባቱን ቢወስዱ ምንም የሚያሰጋቸው ነገር አይኖርም። ክትባቱ ለነፍሰ ጡሮች ጎጂ አይደለም፤ ስለሆነም ነፍሰ ጡር ሴቶች ከበሽታው ለመከላከል ክትባቱን መውሰድ ይኖርባቸዋል።

**የኮቪድ-19 ክትባት ሰዎች መካን እንዲሆኑ አያደርግም**

- አንድ ቀን ልጅ እንዲኖራችሁ ብትፈልጉ የኮቪድ-19 ክትባት መውሰድ ትችላላችሁ። ክትባቱ ወንዶችንም ሆነ ሴቶችን መካን ስለማድረጉ እና ሌሎችም የጎንዮሽ ጉዳት ያመጣል የሚል ምንም ዓይነት ማስረጃ አልተገኘም።

**ኮቪድ-19 ተይዛችሁ ቢሆን እንኳን መከተብ ይኖርባችኋል**

- እስካሁን ድረስ የኮቪድ-19 በሽታ መች እንደሚያልቅ የተረጋገጠ ነገር የለም። እንዲሁም ሌሎች ተስፋፊ በሽታዎች ኮቪድ-19 ከያዛቸው ጋር ያላቸውን ሁኔታ አናውቅም። እኛ የምናውቀው ኮቪድ የተያዘ ሰው ደግሞ ዝንደሚያዝ ነው። ክትባቱ ግን በሕመሙ ክፉኛ ከመሰቃየት ያድናል።

**በመከተብዎ ለኮቪድ-19 በሽታ ሊጋለጡ አይችሉም**

- ክትባቶች በውስጣቸው ኮቪድ-19 በሽታን ሊያመጣ የሚችል ቫይረስ የለውም

**ምንም እንኳን ማጎልበቻ (BOOSTER) መውሰዱ ቢያስፈልግም መከተቡ ደግሞ የበለጠ አስፈላጊ ነው።**

- ለኮቪድ-19 በሽታ ክትባት ዋነኛው መከላከያ ነው። የኮቪድ-19 ክትባት ከከባድ ሕመም፣ የሆስፒታል ታካሚ ከመሆንና በዚሁ ሕመም ጋር በተያያዘ ከሚመጣው የሞት አደጋ ይከላከላል። ማጎልበቻ ክትባት (BOOSTER VACCINATION) መውሰድ የቫይረሱ ተጠቂ ከመሆንና አሁን ከክትባቱ በኋላ ያለዎትን የጤና ሁኔታ እንደተበቀ ማቆየት ይችላል።

**ከክትባት በኋላ የጎንዮሽ ጉዳት የተለመደ እና አይቀሬ ነው።**

- የጎንዮሽ ጉዳቱ ከኮቪድ-19 በሽታ ጋር ሲነፃፀር ኢምንት ነው። ሲከተቡ ሕመም፣ ዕብጠት ወይም የሰውነት መቅላት በተከተቡበት ቦታ ላይ ያሳያል። ራስ ምታት፣ የሕመም ስሜት፣ ድካም እና መለስተኛ ትኩሳት ከተሰማዎ ክትባቱ እየሠራ ነው ማለት ነው። ይኸም ሁኔታ ከአንድ እስከ ሁለት ቀናት ብቻ ይወስዳል። ከክትባቱ በኋላ ባያምዎትም ችግር የለውም። እያንዳንዱ ሰውነት በክትባት ጊዜ የራሱ የሆነ መልስ አለው።

**በመከተብ የሚገኘው ጥቅም ከሚያመጣው ጉዳት ጋር ሲታይ ጥቅሙ ይበልጣል።**

- ጃንሰን ጃንሰን የተባለው ክትባት ሲወሰድ ደም ሊያረጋ ይችላል የሚል ግምት አለ። አስፈላጊው ነገር ግን እንዲህ ያለው ጉዳት በጣም ጥቂት ሲሆን ጉዳቱም ሊታከሙት የሚችል ዓይነት ነው። ባለሙያዎች እንደሚሉት ከሆነ መከተቡ ከሚያመጣው ጉዳት የተሻለ መሆኑን ነው። ወደፊት እየታየ ሁኔታዎች የሚለወጡበት ጊዜ ይመጣል። አሁን ባለው ሁኔታ ግን መጠነኛ ችግር እንዳለው ማወቁ ምን ያህል ለክትባቱ ያለንን ጥያቄ ያሳያል።

ስለ ኮቪድ-19 እያወቅን በመጣን ቁጥር በየጊዜው አዳዲስ ነገሮች እናገኛለን። ይኼ ሁኔታ ሕይወት የሚያድነውን የኮቪድ ክትባት ከመውሰድ ወደ ኋላ አያስብልም።

More to Learn

ስለ ኮቪድ 19 ለማወቅ በጣርን ጊዜ በየጊዜው አዳዲስ ነገሮች እናገኛለን። ይኼ ሁኔታ ሕይወት የሚያድነውን የኮቪድ ክትባት ከመውሰድ ወደ ኋላ አያስብልም።

ስለ ኮቪድ-19 የበለጠ መረጃ ካስፈለገዎ
(www.health.state.mn.us/disease/coronavirus/vaccine/basics.html)

Minnesota Department of Health | health.mn.gov | 651-2021-5000 | 625 Robert Street North PO Box 64975, St. Paul, MN 55164-0975
Contact health.communications@state.mn.us to request an alternate format

**የትርጉም ምንጭ፦** MDH Minnesota Dept. of Health
www.health.state.mn.us/disease/coronavirus/vaccine/basics.html

TAKS Faith Community Health Program.
2601 Minnehaha Ave. MPLS, MN 55406

Translated by Abraham Solomon | Communication Specialist | 5abrahamsolomon@gmail.com | Tel. (612) 275-9418